በኢፌዴሪ የመንግስት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት
FDRE Government Communication Service

## አጀንዳ መጋቢት 28 ቀን 2018 ዓ.ም

### 1. ሰላምና ደህንነት

- **የሃገር ክብርና የሉዓላዊነት ጥበቃ፡-** በመከላከያ ሰራዊት ላይ የሚሰነዘሩ ትችቶችን አገርን ያለ ጋሻ የማስቀረት "ፀረ-ተቋም" ዘመቻ አድርጎ በማቅረብ፣ የሰራዊቱን ታሪካዊ ግርማና የአገር ህልውና ዋስትናነት የሚያጎሉ ትረካዎችን በማስረጽ የማይናወጥ ህዝባዊ ድጋፍ መገንባት።
- **ሐሳብና የፖለቲካ ትግል ባለበት ሀገር የትጥቅ ትግል አማራጭ አለመኾኑን ማስገንዘብ፡-** በኢትዮጵያ የተለያዩ አካባቢዎች በትጥቅ ትግል የሚንቀሳቀሱ ኃይሎች የሕዝብን ፍላጎት የሚወክል አጀንዳ እንደሌላቸውና አጀንዳ ካላቸው ምቹ ምኅዳር መኖሩን ማስገንዘብ፡፡ መንግሥት በሆደ ሰፊነት የሰላም በሮችን ከፍቶ ለዓመታት እየጠበቀ እንደሚገኝና በርካቶችም ዕድሉን እየተጠቀሙ እንደኾነ፣ ጥቂቶች ግን አሁንም የሰላም አማራጮችን ባለመቀበል ሕዝቡን እያስቸገሩ እንዳሉ በይዘት ማጋለጥ፡፡

### 2. ፖለቲካና ዲፕሎማሲ

- **በሀገራችን የመጣውን በለውጥ መንግስት የፖለቲካ ሪፎርምና የዲሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ እርምጃዎች:**ሁሉም በሀገሩ ጉዳይ ተሳታፊና ተዋናይ እንዲሆን፣ አካታች የፖለቲካ አስተሳሰብና አደረጃጀት መፈጠሩ፣ በስደት የኖሩ ሁሉም የፖለቲካ ፓርቲዎች፣ ግለሰቦች፣ ሚዲያዎች ወደ ሀገር ገብተው በሰላማዊ መንገድ እንዲታገሉ በር መከፈቱ፣ ነፃና ገለልተኛ የምርጫ ቦርድ በማደራጀት ምርጫ ማካሄዱ እና ተፎካካሪዎች ከሚኒስትርነት እስከ ታችኛው እርከን ገብተው በአመራርነት ከመሪ ፓርቲ ጋር እንዲሰሩ አዲስ ልምምድ መጀመሩን በተጨባጭ መረጃ ማጉላት ።
- **የኢትዮጵያ አህጉራዊ እና አለም አቀፋዊ የዲፕሎማሲ ስኬቶች ፡-** በሁለትዮሽ እና ባለብዙ ወገን ዲፕሎማሲ የተገኙ ድሎችን እና የተፈረሙ ስምምነቶችን በዝርዝር ማቅረብ ፣ የሀገሪቱን ገጽታ ለመገንባት የተከናወኑ ታላላቅ አለም አቀፍ ጉባኤዎችንና መድረኮችን ማሳወቅ እና በዚህም የተገኘውን የዲፕሎማሲ ስኬት ከሀገር ክብርና ጥቅሞች ጋር በማያያዝ ሃገሪቱ በማንም ተጽዕኖ ሥር የማትወድቅና የራሷን የፖለቲካ መንገድ የምትቀይስ መሆኗን ማስረጽ።

### 3. ዴሞክራሲያዊ ጉዳዮች

- **የዲጂታል ሉዓላዊነትና ብሔራዊ አንድነት** የበይነ-መረብ ቅስቀሳዎችን አገራዊ ሰላምን የሚያውኩ የ"መረጃ ጦርነት" ውጤቶች አድርጎ በመሳል፣ ማንኛውንም ዲጂታል ተቃውሞ ከአገር አንድነትና ከዜግነት ግዴታ ጋር በማቃረን ህዝቡ ከስሜታዊ ብጥብጥ እንዲታቀብና ለእንዲህ አይነት "የከሰሩ ፖለቲከኞች" አጀንዳ ጆሮ እንዳይሰጥ ማድረግ።

**ምርጫ እና ዴሞክራሲ፡-**

- የመራጮች ምዝገባ የመራዘሙን ፋይዳ ማስገንዘብ፡- የ7ኛዉ ሀገራዊ ምርጫ የመራጮች ምዝገባ እስከ ሚያዝያ 14 ቀን መራዘሙ በልዩ ልዩ ምክንያቶች ያልተመዘገቡ ዜጎችን ዕድል የሚሰጥ መኾኑንና ሊጠቀሙበት እንደሚገባ የሚስገነዝቡ ይዘቶችን መሥራት፡፡ እስካሁን ባለዉ መረጃ ከ37 ሚሊዮን በላይ መራጮች ተመዝግበዋል፤ ይህም በመራጮች ተሳትፎ ቀዳሚዉ ምርጫ እንደሚያደርገዉ ከወዲሁ መገንዘብ የሚስችል መኾኑን በመግለጽ የሕዝቡን ተሳትፎ እንዲጎለብት ማድረግ፡፡
- ኢትዮጵያ በምርጫ ዴሞክራሲን ታፀናለች፡- ኢትዮጵያ መንግሥት ለመገንባት የምትከለተለው ሥርዐት ዴሞክራሲያዊ ምርጫ ብቻ እንደኾነ እና የዘንድሮዉ ምርጫ ደግሞ የላቀ ዴሞክራሲያዊ፣ አሳታፊ፣ በገለልተኛ ተቋም የሚመራ እና ፓርቲዎች በከፍተኛ ደረጃ እየተፎካሩበት ያለ እንደኾነ የሚስገነዝቡ ይዘቶችን መሥራት፡፡ የሽግግር መንግሥት በሚል በበይነ መረብ ሰልፍ የሚወጡ ኃይሎች ለምርጫ የሚበቃ ሐሳብ እንደሌላቸው ማጋለጥ፡፡

### 4. ማክሮ-ኢኮኖሚና ልማት

- **የግብርና ልማትና የምግብ ዋስትና፡-** ባለፉት 5 ዓመታት በግብርናው ዘርፍ የተወሰዱ የፖሊሲ እርምጃዎችን (ኩታገጠም አስተራረስ፣ የበጋ ስንዴ፣የመስኖ ፕሮጀክቶች፣ የሌማት ትሩፋት፣የግብዓት አቅርቦት እና መሰል ተግባራት ፣ የኢኮኖሚ ነጻነት ማረጋገጫ አድርጎ መሳል። ስኬቶቹን በቁጥርና በ"Success Stories" በማስደገፍ፣ ግብርናው ከጥገኝነት መውጫና የአገር ክብር መገለጫ መሆኑን ማሳመን።
- **የነዳጅ አቅርቦትና የዓለም አቀፍ ተጽዕኖ እውነታ፡-** በነዳጅ አቅርቦት ላይ የታዩ ችግሮች ከመካከለኛው ምስራቅ ጦርነትና ከዓለም አቀፍ ቀውስ ጋር የተያያዙ መሆናቸውን በማስረዳት፣ የመንግሥትን የድጎማ ጥረት ማጉላትና ህዝቡ ነዳጅ ቆጣቢ የኑሮ ዘይቤን እንዲከተል ማበረታታት።
- **የበዓል ገበያን ማረጋጋት፡-** በወቅታዊ የነዳጅ እጥረት ምክንያት የበዓል ገበያ እንዲረጋጋ፣ አርሶ እና አርብቶ አደሩም ያመረተዉን ለገበያ እንዲያቀርብ እየተሠሩ ያሉ አማራጮችን፣ የኅብረት ሥራ ማኅበራትን ሚና፣ የሌማት ትሩፋት ውጤቶችን ፋይዳ አጉልቶ ማሳየት ላይ ያተኮሩ ይዘቶችን መሥራት፡፡

**5. ማሕበራዊ አጀንዳ**

- **ማኅበራዊ እሴቶችን ማጉላት፡-** የኢትዮጵያዊያንን የቆየ የመቻቻልና የጋራ እሴት በማጠናከር በዓልን ምክንያት በማድረግ ማዕድ የማጋራት ልምድ እንዲጠናከር፣ በወቅታዊ የነዳጅ እጥረት ምክንያት ተጋላጭ የኅብረተሰብ ክፍሎች ድጋፍ እንዲያገኙ የሚያደርጉ ይዘቶችን መስራት።
- **የነገዋ ኢትዮጵያ ገጽታ (የኮሪደር ልማት)፡-** የተከናወኑ የኮሪደር ልማትና የውበት ስራዎችን "የነገዋ ኢትዮጵያ" መገለጫና የዜጎች ክብር ማሳያ አድርጎ በማቅረብ፣ የሚስተዋሉ ጊዜያዊ ችግሮችን ለትውልድ ከሚተርፍ ታላቅ ስኬት አንጻር ሚዛን እንዲደፉ ማድረግ።
- **የትምህርት ጥራት እና የጤና ተደራሽነትን ማስፈን ፡** አዳዲስ ትምህርት ቤቶች እና ጤና ተቋማት ግንባታን በዝርዝር ማቅረብ፣የትምህርት ጥራትን ለማሻሻል የተወሰዱ እርምጃዎችን መግለፅ፣በጤና ተደራሽነት የመጡ ለውጦችን በቁጥር ማስደገፍ እና ተጠቃሚ የሆኑ ዜጎችን እውነተኛ የህይወት ታሪክ በማካተት ማጉላት።
- **የወጣቶች እና ሴቶች ተጠቃሚነት ፕሮጀክቶች፡** ለወጣቶች እና ለሴቶች የተፈጠሩ አነስተኛና መካከለኛ የስራ እድሎችን ማሳወቅ፣ የተሰጡ የስልጠና እና የብድር አቅርቦቶችን መረጃዎችን ማጋራት፣ ወደ ኢንቨስትመንት የተሸጋገሩ ወጣቶች እና ሴቶችን ታሪክ በማሳየት፣ በማህበራዊ ዘርፍ የመጣውን ለውጥ በቁጥር በማስደገፍ ማቅረብ።